የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት
ALL ETHIOPIA UNITY PARTY

☎ +251-111 55 35 06, +251-111 55 17 89, +251-116-55 12 56 Fax. +251-111 55 31 55
17013 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Abeba Ethiopia, Website:- www.kaeup.org e-mail:-[illegible]@ethionet.et

ቁጥር
Ref. No. 001/3/22/203
ቀን
Date 24/01/2003

## I. በኃይል የሕዝብን ድምፅ የዘረፈው ኢህአዴግ የሚመሠርተው መንግሥት ሕጋዊ ባለመሆኑ ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም!

ህዳር 15 ቀን 2002 ዓ.ም ተጀምሮ ግንቦት 15 ቀን 2002 ዓ.ም በሕዝብ ድምፅ-ተብዬው የተጠናቀቀው የይስሙላ ምርጫ የኢህአዴግ ካድሬዎች በተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች እጩ ተወዳደሪዎች፣ የምርጫ ታዛቢዎች እና ደጋፊዎች ላይ ማስፈራራት፣ ድብደባ፣ አሥራትና ግድያ የፈጸሙበት አሳፋሪ የኢትዮጵያን ሕዝብ መልካም ባሕሪ፣ ሰላም ፈላጊነት እና ለነፃነቱ ቀናኢነት የሚወክሉ አይደሉም፡፡ ይህም ብቻ አይደለም፡፡

ግንቦት 15 ቀን 2002 ዓ.ም የተከናወነው ምርጫ-ተብዬው ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ታዛቢዎች ያልተሳተፉበት፣ በተቃራኒው ተደብድበው የተባረሩበት፣ የታሰሩበት እና በሁሉም አካባቢዎች ምርጫውን እንዳይታዘቡ የተከለከሉበት ነበር፡፡

በተወሰኑ የአዲስ አበባ የምርጫ ጣቢያዎች እና ሌሎች ከተሞች ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ታዛቢዎች በተገኙበት ደግሞ ምርጫው መካሄድ ከሚገባው ሰዓት በፊት ኢህአዴግ ደጋፊዎቹን አስቀድመው ወደ ምርጫ ጣቢያዎች መጥተው እንዲመርጡ በማድረጉ የድምፅ ኮሮጆዎች በተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ታዛቢዎች ሳይፈተሹ ምርጫው እንዲከናወን ተደርጓል፡፡

የኢህአዴግ ካድሬዎች በቡድን በቡድን ተደራጅተው ከምርጫ ጣቢያዎች ጀምሮ በ10 እና በ15 ሜትር ርቀት ላይ በመገኘት ቀደም ሲል በቡና ጠጡ ወቅት ኢህአዴግን እንዲመርጡ ቃለ መሃላ ያስፈጸሙአቸውን አቅመ ደካማ የሕብረተሰባችንን ክፍል ኢህአዴግን እንዲመርጡ ተቆጣጥረዋቸዋል፡፡ የመጡት የተፈረመ የምርጫ ካርድ ተሰጥቶአቸው ኮሮጆው ውስጥ እንዲከቱ፣ ከምርጫ ጣቢያው የተቀበሉትን የምርጫ ካርድ ደግሞ ለኢህአዴግ እንዲመልሱ የተደረገበት፣ ለምርጫው ያልመጡ ደግሞ በስልክ ተጠርተው "እየጠበቅናችሁ ነው፣ ኑና ኢህአዴግን ምረጡ እንጂ" ተብለው ተገድደው የመረጡበት ትያትር የታየበት ቀን ነበር ግንቦት 15 ቀን 2002 ዓ.ም፡፡

የእነዚህ ድርጊቶች ዓላማና ግብ ግልጽ እና አንድ ነበር፡፡ በአንድ በኩል ኢህአዴግ በካድሬዎቹ አማካኝነት በተዘጋጀ የሕዝብ ድምፅ ኮሮጆውን ለመሙላት እንዲያመቸው ያደረገው፣ የለመደውና የኖረበት የተንኮል አሠራር ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የተወሰነ የሕብረተሰባችንን ክፍል በማስፈራራት እንዲመርጡት ያስገደደበት ነበር፡፡

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት "መኢአድ"
ALL ETHIOPIA UNITY PARTY (AEUP)

ግንቦት 16 ቀን 2002 ዓ.ም ኢህአዴግ 99.6 በመቶ የሕዝብ ድምፅ አግኝቼ አሸነፍኩ ብሎ ካለወትሮው 24 ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የምርጫውን ውጤት ያወጀው ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነበር፡፡

መኢአድ በተለያዩ የሀገራችን አካባቢዎች ባደረገው የናሙና ዳሰሳ ባገኘው መረጃ መሠረት ኢህአዴግ 99.6 በመቶ የኢትዮጵያን ድምፅ አገኘሁ ሲል ዘርፎ መሆኑን የማያውቅ ኢትዮጵያዊ እንደሌለ ተረጋግጧል፡፡ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የመረጠውን የሚያውቅ ከመሆኑም በላይ ሌላው ኢትዮጵያዊ ጉረቤቱ፣ ወዳጅ ዘመዱ፣ የመረጠውን ተነጋግረው ሁኔታውን ያውቃሉና! ኢህአዴግን እንዲመርጡ የተገደዱትም በእየ-አካባቢው እሮሮ እያሰሙ ነው፡፡

ኢህአዴግ ላለፉት 18 ዓመታት የመንግሥትን ሥልጣን በኃይል ይዞ እንደቆየ ሁሉ፣ በምርጫ 2002 ዓመተ-ምህረትም የሕዝብን ድምፅ ዘርፎ ዛሬም የመንግሥት ሥልጣን በኃይል አቋቁሞአል፡፡

የተቋቋመው የኢህአዴግ መንግሥት የሕዝብ ሥልጣን ይሁንታ የሌለው በመሆኑ ሕጋዊ መንግሥት አይደለም፡፡ በመሆኑም ማንም ለግል ነፃነትም ሆነ ለቡድን ነፃነት ቀናኢ የሆነ፣ ለሕዝብ ድምፅ አክብሮት ያለው፣ ለሕግ የበላይነት ክብር ያለው፣ እንዲሁም ለዲሞክራሲ ግንባታ እና ለመልካም አስተዳደር በመታገል ላይ ያለ ወይም በመልካም አስተዳደር የሚያምን መንግሥት ኢህአዴግ ያቋቋመው መንግሥት የኃይልና የፕሮፓጋንዳ ውጤት እንጂ ሕጋዊ እና እውነተኛ ያልሆነ፣ የሕዝብ ይሁንታ የሌለው መንግሥት በመሆኑ እውቅና ሊቸረው አይገባም፡፡

የዳያስፖራ ኢትዮጵያውያን ደጋፊዎቻችንና ማናቸውም ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ኢህአዴግ የመሠረተው መንግሥት ሕጋዊ ባለመሆኑ በያላችሁበት ሀገር በሰላማዊ ሰልፍ ወይም በሌሎች አመች በሆኑ መንገዶች የምታወጡት የተቃውሞ መግለጫ ያላችሁበት መንግሥታት እና ሕዝብ እንዲሁም የዓለም ሕብረተሰብ ከመላው የኢትዮጰያ ሕዝብ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) ጎን በመቆም የሕዝባችሁን ነፃነት ከአምባገነኑ ኢህአዴግ መዳፍ ለማላቀቅ በሚደረገው ሰላማዊ ትግል ወሳኝ አስትዋጽኦ አለው፡፡

## II. <u>ሕዝብን ማሳሳት መሞከር መጨረሻው ውድቀት ነው!</u>

ኢህአዴግ መኢአድ “በአምስት ዓመቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ  ላይ እንዲሳተፍ መኢአድን ብጠራው በደብዳቤ ካልጠራሽኝ በቀር አልሳተፍም ብሏል” እያለ ሰሞኑን በሚቆጣጠራቸው ብሔራዊና የአካባቢ ሬዲዮኖች ሲለፍፍ እንደነበረ ደርሰንበታል፡፡

እዚህ ላይ ሦስት ነገሮች ማንሳት እንፈልጋን፡፡ አንደኛ፣ መኢአድ እውነት በደብዳቤ ካልተጠራሁ በቀር ወይስ በሌላ ምክንያት በስብሰባ አልገኝም አለን? ሁለተኛ፣ ኢህአዴግ መኢአድን ለምን በደብዳቤ መጥራት ፈራ? ሦስተኛ፣ ኢህአዴግ ቀደም ሲል ያደርግ እንደነበረው በቴሌቪዥን መሆኑ ቀርቶ በሬዲዮ ማስነገርን ለምን መረጠ? እነዚህን ተራ በተራ መልስ እንሰጥባቸዋለን፡፡

ALL ETHIOPIA UNITY PARTY (AEUP)

መኢአድ እውነት በደብዳቤ ካልተጠራሁ በስብሰባ አልገኝም ብሏል? መኢአድ ኢህአዴግ በጠራው ስብሰባ ላይ ላለመገኘት ከዚህ የበለጠ ብዙ በቂ የሆኑ ምክንያቶች ስላሉት ስልክ የተደረገለት የመአአድ ሥራ አመራር አባል የሰጡት መልስ የመኢአድ የሥራ አስፈፃሚ በወሰነው መሠረት “በደብዳቤ ስላልጠራችሁን መልስ ልንሰጥ እንቸገራለን” የሚል ነበር። ስለዚህ ኢህአዴግ ለምን ያልተባለውን ተብሏል ማለት አስፈለገው? መልሱ ግልጽ ነው። ከዚህ ዝቅ ብለው ያገኙታል።

ኢህአዴግ መኢአድን ለምን በደብዳቤ መጥራት ፈራ? በመሠረቱ ለዚህ አብይ ሀገራዊ ጉዳይ የተጠራው መኢአድ ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ናቸው። እንዲህ ዓይነቱ አብይ ሀገራዊ ጥሪ እንደ ተራ ጥሪ በቃል ሳይሆን በደብዳቤ መጠራት እንዳለበት የሥራ ሥነ-ምግባር ይጠይቃል። ሀገራችንን ጨምሮ በዓለም ዙሪያ የሚሰራበት ሥርዓት ይኸው አሠራር ነው።

ኢህአዴግ ለምን መኢአድን በደብዳቤ ለመጥራት እንደፈራ ባናውቅም መኢአድ በስብሰባው ላይ የማይሳተፍበት ዋናው ምክንያት ኢህአዴግ ግንቦት ወር ውስጥ ለተሰጠው “The Saga 0f 23 May 2010 Federal and Regional Elections and the Way Forward” የመኢአድ ጽሑፍ መልስ ሳይሰጥ መኢአድ ኢህአዴግ ጋር የሚሰበሰብበት ምክንያት የለውም። በዚህ ጽሑፍ ውስጥ መኢአድ ለኢህአዴግ ያቀረበውን ጥያቄ በማጠናከር ነሐሴ 18 ቀን 2002 ዓ.ም ሌላ ተጨማሪ ሦስት ጽሑፎች በማውጣት ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥቷል። በጋዜጣው መገለጫ ላይ ከተሳተፉት ውስጥ ክቡር አቶ በረከት ስምኦን በቦርድ ሰብሳቢነት የሚመሩት የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት የተገኘ ሲሆን ሶስቱም የመኢአድ ሰነዶች ተሰጥተውታል። ከዚህም በላይ መኢአድ ቀደም ሲል ለኢህአዴግ ያቀረባቸውን ጥያቄዎች አስመልክቶ ከክልል ከመጡት የሥራ አስፈጻሚ አባላቱ ጋር በመሆን ከሦስት ሰዓት ያላነሰ ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥቶበታል። ይህም በመንግሥት የሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ተቀድቷል። ኢህአዴግ በተለያዩ ጊዜ ለቀረበለት ለእነዚህ ጥያቄዎች ‘ጆሮ ዳባ ልበስ’ ባለበት ሁኔታ መኢአድን ለስብሰባ መጥራቱ አግባብ ባለመሆኑ መኢአድ የማይቀበለው ጥሪ ነው።

ኢህአዴግ ቀደም ሲል አዝወትሮ ሲያደርግ ከነበረው ከቴሌቪዥን ይልቅ ለምን ስለመኢአድ የስብሰባ ጥሪውን ያለመቀበል ጉዳይ በሬዲዮ ማስነገር መረጠ? መልሱ ከላይ መኢአድ ያላለውን ብሏል በማለት ኢህአዴግ ለሬዲዮ ከሰጠው መግለጫ ጋር አንድ ነው። እንደሚታወቀው የመኢአድ መሠረት ብዙኃኑ ሬዲዮ ተጠቃሚ ሕዝብ ነው። በመሆኑም ኢህአዴግ እንደለመደው በደጋፊዎቻችን ዘንድ መኢአድን ለማሳጣት የተጠቀመበት ታክቲክ ነው። ይሁን እንጂ ደጋፊዎቻችንና ሕዝባችን ቀደም ሲል በመኢአድ ለኢህአዴግ የተሰጠው ቅድመ ሁኔታ ከእነርሱ ጋር በመመካከር የተፈፀመ እና በጽሑፍም የደረሳቸው በመሆኑ በቀላሉ አይወናበዱም። ስለዚህ መኢአድ ያላለውን ኢህአዴግ ብሏል በማለት ሕዝብን ማሳሳት እራስን ማጋለጥ እና ለውድቀት መዳረግ እንጂ መኢአድን ከራሱ ህዝብ ጋር ማጣላት እንደማይቻል ኢህአዴግ አስቀድሞ በተገነዘበ ነበር!

በነገራችን ላይ እሁድ መስከረም 23 ቀን 2003 ዓ.ም የወጣው የሪፖርተር ጋዜጣ ቅፅ 16 ቁጥር 04/1088 ደግሞ አንድ አስገራሚ ነገር ይዞ ወጥቷል። ኢህአዴግ  መድረክን ለውይይት የሚጠራው የሥነ-ምግባር ደንቡን ሲፈርም ነው አለ ተብሏል።

የፖለቲካ ፓርቲዎች የሥነ-ምግባር አዋጅ ቁጥር 662/2002 ዓ.ም ሕግ ሆኖ የወጣ በመሆኑ በማንም ፓርቲ፣ ድርጅትና ግለሰብ ተፈጻሚ ነው። መድረክ ኢህአዴግ በሚያዘጋጀው ስብሰባ ላይ ለመገኘት ይኽንን ሥነ-ምግባር ተቀብያለሁ ብሎ መፈረም አያስፈልገውም። መድረክ እንኳን ኢህአዴግ በሚጠራው ስብሰባ ላይ ለመገኘት ቀርቶ ለምርጫ 2002 ዓ.ም ሰነዱን መፈረም ሳያስፈልገው ተወዳድሯል እኮ! ስለዚህ ኢህአዴግ መድረክን ለስብሰባ የማይጠራበት ሌላ ምክንያት ይፈልግ እንጂ ከላይ የተመለከተው የፓለቲካ ፓርቲዎች የሥነ-ምግባር አዋጅ መድረክን ሆነ ሌላ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም ሌላ አካል ለስብሰባ እንዳይጠራ የሚያግድ አንቀጽ የለውም።

በተቃራኒው ግን ኢህአዴግ የሥነ-ምግባር ሕጉ ያስቀመጣቸውን ሁሉንም ስድስት ጥሰቶች ማለትም ከአንቀጽ 27 እስከ 32 ያሉትን ክልከላዎች  በምርጫ 2002 ዓ.ም ወቅት ጥሷቸው ከሕግ በላይ ሆኖ ዛሬ ድረስ አልጠየቅባቸውም ብሎ በጉልበቱ መንግሥት አቋቁሟል። በመሆኑም የኢትዮጵያ ሕዝብ የፍትህ ያለህ እያለ ነው! ኢህአዴግ ያቋቁመውም መንግሥት ህጋዊ ባለመሆኑ እውቅና ሊሰጠው አይገባም ይላል። በተቃራኒው ኢህአዴግ የህዝብን ድምፅ እንዲያከብር እና ዳግመኛ ምርጫ እንዲያካሄድ የጥሪ ደወል በማሰማት ላይ ይገኛል።

ከማክበር ሰላምታ ጋር

ያዕቆብ ልኬ
የመኢአድ የውጭ ጉዳይ ኃላፊ